# ክርስቲያናዊ ጾም

*ጾም ቃሉ የግእዝ ሆኖ ፍችው ጦም ማለት ነው። ጦም ማለት ሰውነትን ከመብል ከመጠጥና ከክፉ ስራ ሁሉ መከልከል ማለት ነው። የጦም ጊዜ ራስን የማዋረድ የኃዘን የጸሎት የንስሐና የኑዛዜ ጊዜ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።*

1. *«በአምላካችን ፊት ራሳችንን እናዋርድ ዘንድ፥ ከእርሱም የቀናውን መንገድ ለእኛና ለልጆቻችን ለንብረታችንም ሁሉ በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጦም አወጅሁ ስለዚህም ነገር ጦምን፤ ወደ እግዚአብሔርም ለመንን እርሱም ተለመነን።» ዕዝራ* 8፥21

2. *«ይህንን ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ አያሌ ቀንም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፥ እንዲህም አልሁ፥ አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ ለሚወዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንንና ምህረትን የምትጠብቅ ታላቅና የተፈራህ አምላክ ሆይ በአንተ ላይም ያደረግነውን የእስራኤልን ኃጢአት እናዘዝልሃለሁ፤ እኛ በድለናል እኛም በአንተ ላይ እጅግ ክፉ ሠርተናል» ነህ.* 1፥4-7

3. *«ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኘ ስጦም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አቀናሁ። ወደ አምላኬም ወደ እግዚአብሔር ጸለይሁ ተናዝዤም እንዲህ አልሁ ኃጢአትን ሠርተናል በድለንማል ክፋትንም አድርገናል አምጸንማል ከትእዛዝህና ከፍርድህም ፈቀቅ ብለናል» ይላል። ዳንኤል* 9፥3-20

*በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት የጦም ጊዜ በንስሃ የመመለስና በኃጢአት የመናዘዝ ራስን የማዋረድና የጸሎት ጊዜ ነው ማለት ነው።*

## የጾም ሰዎች

*ጾምን የሚጦሙ ሰዎች በሁለት ይመደባሉ። እነሱም፥*

1. *የጾም ጊዜያቸው እስኪፈጸም ድረስ ያለምንም እህል ውሃ በባዶ ሆድ የሚጦሙ ሲሆኑ*

2. *ከጥሉላት ማለት ከሥጋ ከቅቤና ከእንቁላል እንዲሁም ከሚያሰክር መጠጥ በመከልከል እስከ ተወሰነ ሰዓት በባዶ ሆድ ቆይተው ሰዓታቸው ሲደርስ ለሥጋ ኃይል ሰጭ ያልሆነ መናኛ ምግብ በመመገብ የሚጦሙ ናቸው። ለዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች አሉ።*

### *ያለ ምንም እህል ውሃ*

1. *«እግዚአብሔርም ሙሴን በእነዚህ ቃሎች መጠን ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው። በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ እንጀራም አልበላም ውሃም አልጠጣም በጽላቶቹም አሥሩን የቃል ኪዳን ቃሎች ጻፈ» ዘጻ* 34፥27 *ሙሴ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ያለምንም እህል ውሃ የጦመው የእግዚአብሔር ትእዛዛት የተጻፉባቸው ሁለቱን ጽላቶች ከመቀበሉ በፊት ስለጽላቶች ነው።*

2. *እስራኤል በፋርስ ባቢሎን በስደት ላይ እንዳሉ ጠላት ተነስቶባቸው በያሉበት ታድነው እንዲገደሉ በተወሰነባቸው ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከስደተኞች መካከል የንጉሡ ሚስት ለመሆን በበቃች አስቴር በምትባል ቅድስት ሴት አማካኝነት ሦስት ቀንና ሶስት ሌሊት እስራኤል በያሉበት እህል ውሃ ሳይቀምሱ ጦመው በይግባኝ የሞት ፍርዱ ወደ ነጻነት ተለውጦላቸዋል። መጽ አስቴር* 4፥13-17

3. *የነነዌ ሰዎች በዮናስ ስብከት እንስሳት እንኳ ሳይቀሩ ያለምንም እህል ውሃ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በመጦማቸው እግዚአብሔር ይቅርታውንና ምሕረቱን ልኮላቸዋል። ዮናስ* 3፥1-10

4. አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣውና በሥጋ የተገለጠው ስለ ሁለት ዐበይት ነገሮች ነው። ይኸውም 1ኛ ራሱን መስዋእት አድርጎ እኛን ለማዳን ሲሆን 2ኛው እኛ ክርስቲያኖች ማድረግ የሚገባንን መልካም ነገር ሁሉ ሠርቶ ሊያሳየን ለአርአያነትና ለምሳሌነት ነው። አርአያና ምሳሌ ሆኖ ካሳየን ነገሮች ውስጥ አንዱ ጦም ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በጦመ ጊዜ ያለምንም እህል ውሃ ነው። ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል

«ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ። ፈታኝም ቀርቦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው። ኢየሱስም መልሶ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በወጣ ቃል ሁሉ እንጅ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፏል አለው» ይላል። ማቴ 4፥1-5 ሉቃ 4፥1-14

እንግዲህ እስካሁን የጠቀስናቸው በሙሉ አቅም ላላቸውና ያለምንም እህል ውሃ መጦም እንፈልጋለን ለሚሉ ሰዎችና ያለምንም እህል ውሃ ለሚጦመው ጦም መረጃዎች ናቸው። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በዚህ የጦም ስልት የሚጠቀሙ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ያውም ቢሆን በግል ደረጃ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ከትንሳኤ ዋዜማ፣ ከቀዳም ስዑርና ከአንዲት ቀን ከገሀድ ጦም በቀር ያለ ምንም እህል ውሃ የሚጦም ጾም የለም።

***<u>በመናኛ ምግብ</u>***

እስካሁን ድረስ ያለምንም እህል ውሃ ለሚጦመው ጦም ስንነጋገር ቆይተናል። አሁን ደግሞ ሥጋን የሚያፋፋና ለሥጋ ኃይል ሰጪ ከሆኑ ከጥሉላት ማለትም ከሥጋ፣ ከቅቤና ከማለፊያ እንጀራ እንዲሁም ከሚያሰክር መጠጥ በመከልከል በመናኛ ምግብ ስለሚጦመው ጦም ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን እንጠቅሳለን።

1. «በዚያም ወራት እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርሁ። ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም፥ ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይት አልተቀባሁም» ይላል። ዳን 10፥2። በመጽሐፈ ነህምያ 1፥4 ለይ የጦም ጊዜ ማለት የኃዘን ጊዜ ማለትም የጦም ጊዜ ማለት መሆኑን እያስታወሰን ይህ ነቢይ (ዳንኤል) በምዕራፍ 9፥3 ላይ «ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ መጾም ጀመርሁ» ካለ በኋላ በምዕራፍ 10፥2 ላይም ደግሞ ይህ የጦም ጊዜ የኃዘን ጊዜ እንደሆነና ቀኖቹም ሦስት ሳምንታት እንደሆኑ ገልጦልናል። ታዲያ በነዚህ ሦስት ሳምንታት ውስጥ ሥጋና ማለፊያ እንጀራ አልበላሁም ጠጅም በአፌ አልገባም በማለት በጦም ጊዜ ሥጋንና ሥጋ ነክ የሆኑ ነገሮችን እንዲሁም ማለፊያ እንጀራና የሚያሰክር መጠጥን ለመተዋችን መረጃና መሠረት ሆኖልናል።

2. «እንዳለፈ ጥላ አለቅሁ እንደ አንበጣም እረገፍሁ ጉልበቶቼ በጦም ደከሙ ሥጋየም ቅቤ በማጣት ከሳ ነፍሴን (ሥጋየን) በጾም አስመረርኋት» ይላል። መዝ 108፥23-25፤ መዝ 68፥10 ይህን ቃል የተናገረውና በተግባር የፈጸመው ቅዱስ ዳዊት ነው። በዚህ ቃል መሠረት «ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ ሥጋየም ቅቤን በማጣት ከሳ ሲል በጦም ጊዜ ቅቤንና ቅቤ ነክ የሆኑ ነገሮችን ላለመብላታችን በቂ መረጃ ነው።

ለመንፈሳዊ እንቅስቃሴያችን ሁሉ መሠረታችን መጽሐፍ ቅዱስ በመሆኑ በጾማችን ጊዜ ያለ ምንም እህል ውሃ መጾም እንችላለን ለሚሉ ጠንካሮች መረጃዎች አይተናል።

# <u>እውነተኛ ጾም</u>

«ቦኑ ዘጾምክሙ ሊተ ጾምሰ አኮ ጸዊም እምኅብስት ወማይ ባህቲቱ ይጹም ልሳንክሙ እምነገረ ውዴት ...መኮንነ ዘኢትክል ትጹም እመባልእት ጹም እንከ እምኅሊናት እኪት» ዘካ 7፥5 ስንክ ታኅ 13 ፊለክ 240

ይህም ማለት ፥በእውነትም ጾምን ጾማችሁለኝን? ከሆነስ ጾም ማለት ከመብል ከመጠጥ ብቻ አይደለም እንደበታችሁን ከነገር ሥራ ከሐሜት ከመጥፎ ቃልና ንግግር እንዲሁም ሰውነታችሁን ከክፉ ሃሳብና ከኃጢአት ሁሉ ከልክሉ ማለት ነው።

በኢሳይያስ 58፥3-13 ደግሞ እንዲህ ይላል፥ «ስለምን ጾምን አንተም አልተመለከትከንም ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን አንተም አላወቅህም ይላሉ። እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፤ ሠራተኞቻችሁን ሁሉ ታስጨንቃላችሁ፤ እነሆ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን? ሰውስ ነፍሱን የሚያዋርደው እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? በዉኑ ራሱን እንደ እንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን? በውኑ ይህን ጾም በእግዝአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን? እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቁ ዘንድ የተገፉትንስ አርነት ትሰዱ ዘንድ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? እንጀራህንስ ለተራበ ትቆርስ ዘንድ፥ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ ከሥጋ ዘመድህስ እንዳትሸሸግ አይደለምን? የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፤ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል። የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል፥ የዚያን ጊዜ ትጣራለህ እግዚአብሔርም ይሰማሃል ትጮሃለህ እርሱም እነሆኝ ይላል፤ ከመካከልህ ቀንበርን ብታርቅ፥ ጣትህንም መጥቀስ ብትተው፥ ባታንጎራጉርም፣ ነፍስህንም ለተራበ ብታፈስስ የተጨነቀውንም ነፍስ ብታጠግብ ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል፤ እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ ይመራሃል ነፍስህንም ከመለካም ነገር ያጠግባል አጥንትህንም ያጠናል፥ አንተም እንደሚጠጣ ገነት ውሃውም እንደማያቋርጥ ምንጭ ትሆናለህ ከዱሮ ዘመን የፈሰሱት ሥፍራዎች ይሠራሉ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል አንተም ሰባራውን ጠጋኝ የመኖሪያ መንገድን አዳሽ ትባላለህ።»

## <u>ጾምና ቀኖና</u>

ቀኖና ማለት ሥርዓትና ሥርዓት መወሰኛ ማለት ነው። የአዲስ ኪዳን ጾም መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፥ የጾም ብዛት፣ የጾም ምግብ፣ ሰዓትና መቼ እንደሆን እንደሌላው የቤተ ርስቲያን ሥርዓት ሁሉ የሚወሰነው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና የተወሰኑ ሰባት የጾም ወራት አሏት።

1ኛ) ዐቢይ ጾም (አርባ ጾም)

ይህ ጾም በማቴ 4፥1 እና በሉቃ 4፥1 እንደተጻፈው ጌታ ራሱ የጾመው «አርባ ጾም» የሚባለው ነው። አርባ ጾም የተባለበት ምንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ምንም ሳይቀምስ ለአርባ ቀናት አርባ ሌሊት ስለጦመው ነው።

ዐቢይ (ትልቅ) የተባለበት ዲያቢሎስ ድል የሆነበት የኃጢአት ሥሮች የሚነቀሉበት ስለሆነ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ርስቶስ የጦመው አርባ ቀን ብቻ ነው። ነገር ግን ከጌታ ጦም ማለትም ከአርባው ቀን በፊት አንድ ሳምንት ከአርባው ቀን በኋላ አንድ ሳምንት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተጨምሮ ዐቢይ ጾም ስምንት ሳምንቶች (55 ቀኖች) አሉት። ከእነዚህ ቀኖች ውስጥ ሰባት ቅዳሜዎችና ስምንት እሑዶች ይገኛሉ። ሲደመሩ አሥራ አምስት ይሆናሉ። እነዚህ አሥራ አምስት ቀኖች ቅዳሜና እሑድ በመሆናቸው ከሥጋና ከቅቤ በቀር ጦም አይጦምባቸውም። ስለዚህ እነዚህን አሥራ አምስት ቀኖች እንደ ጦም ባለመቁጠር ቀኑ አርባ ቀን ብቻ መሆኑን የቀደሙ አባቶች ተናግረዋል። ከአርባው ቀን በፊት አንድ ሳምንት ከአርባው ቀን በኋላ አንድ ሳምንት የጨመሩትም ለዚህ ነው።

ዐቢይ ጾም የጌታ ጾም በመሆኑ ዐቢይ ጦምን ስንጦም ጌታችን ኢየሱስ ርስቶስ ለእኛ ያደረገልንን መልካም ነገር እና ስለእኛ የተቀበለውን መከራ ሁሉ እያሰብን መሆን እንዳለበት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተናግረዋል። ከዚህም የተነሳ በዐቢይ ጾም ለእያንዳንዳቸው እሑዶች ቅዱስ ያሬድ ስም እንደሰጣቸው ጾመ ድጓ ይናገራል።

1ኛ እሑድ ጾመ ሕርቃል ይባላል። የመጀመሪያው እሑድ ከቅዱስ ያሬድ ሌላ ተጨማሪ ታሪክ አለው። ሕርቃል የቢዛናታይን ንጉሥ የነበረ ሰው ነው። በዘመኑ የፋርስ ኃያላን በኃይል ኢየሩሳሌምን ወረው የጌታን መስቀል ማርከው ወስደው ነበር። ይህ ንጉሥ እግዚአብሔርን ኃይል በማድረግ ወደ ፋርስ ዘምቶ መስቀሉን ነጥቆ ወደ ኢየሩሳሌም በመመለስ ክርስቲያኖችን አስደስቷል። ስለዚህ እግዚአብሔር በሕርቃል አድሮ የሠራውን ድንቅ ሥራና ለዚህ ድንቅ ሥራ ምክንያት የሆነውን ንጉሥ ሕርቃልን ለማሰብ ጾመ ሕርቃል ተብሎአል። በሌላ በኩል ደግሞ ዋናው የጌታን አርባ ጾም ለመቀበል ርስቲያኖች ሰውነታቸውን በጾም የሚያለማምዱበትና የመዘጋጃ ሳምንት ነውም ይባላል።

1ኛ እሑድ ... ይህን እሑድ ቅዱስ ያሬድ ዘወረደ ብሎታል። ያለበትም ምንያት አምላክ ከሰማይ መውረዱን መስቀሉንና መሞቱን ለመናገር ነው።

2ኛ እሑድ ... ይህ እሑድ ቅድስት ይባላል። በተለይ ስለ ዕለተ ሰንበት ክብርና ቅድስና ስለሚነገር ነው።
3ኛ እሑድ ምኩራብ ይባላል። ጌታ በዕለተ ሰንበት ወደ ምኩራብ (ቤተ ጸሎት) እየገባ ወንጌል ማስተማሩን ለማሰብና ለመናገር ነው። ..... ማቴ 12፥9

4ኛው እሑድ መጻጉዕ ይባላል። መጻጉዕ ማለት በሽተኛ ማለት ነው። ስለዚህ ጌታ ድውያንን መፈወሱን፣ አጋንንትን ከበሽተኞች ማባረሩን፣ እውራንን ማብራቱንና ተአምራትን ማድረጉን ለማሰብ ነው። ... ዮሐ 5፥1-47 ። ዮሐ 9፥1-41

5ኛው እሑድ ደብረ ዘይት ይባላል። ደብረ ዘይት በተባለ ተራራ ላይ ጌታ ስለ ዓለም መጨረሻ፣ የዓለም መጨረሻም ሲቃረብ ስለሚከሰቱ ምልቶችና ስለ ምጽአቱ የተናገረውን መለኮታዊ ቃል እንዲያስብ ለማድረግ ነው። ...... ማቴ 24፥3-51

6ኛው ገብር ሄር ይባላል። ገብር ሄር ማለት ደግ፣ ታማኝ፣ አገልጋይ ማለት ነው። ይህም ጌታ ለታማኝ አገልጋዮች ወደፊት የሚሰጣቸውን ሰማያዊ ስጦታ በምሳሌ ያስረዳውን ትምህርት ምን ጊዜም ለማሰብ ነው። ... ማቴ 25፥14-31

7ኛው እሑድ ኒቆዲሞስ ይባላል። በሌሊት ወደ ጌታ እየመጣ ይማር የነበረውን የአይሁድ ባለ ሥልጣን ኒቆዲሞስንና ጥምቀት ሁለተኛ ልደት መሆኑን የምናስታውስበት ነው። .... ዮሐ 3፥1-16

8ኛው እሑድ ሆሳዕና ነው። ጌታ በአህያ ውርንጭላ ላይ ሆኖ «ሆሳዕና በአርያም» እየተባለ ወደ ቤተ መቅደስ የገባበት ዕለት መታሰቢያ ነው። .... ማቴ 21፥1-16

ከሆሳዕና ጀምሮ እስከሚቀጥለው እሑድ ማለትም እስከ ትንሣኤ ድረስ ያለው ሰባት ቀን ሕማማት ሲባል በዚህ ሳምንት የጌታን መከራና ሞት የሚያስታውሱ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነበባሉ። ስግደትም በየተወሰነው ሰዓት ይሰገዳል። አዳም ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ የኖረውን የጨለማና የመከራ ዘመን ለማስታወስ መንበረ ታቦቱ በጥቁር ልብስ ይሸፈናል። ካህናቱ ለአገልግሎት የሚለብሱት ልብሰ ተህኖም ጥቋቁር ነው።

## <u>*ዕለተ ሐሙስ*</u>

ከስቅለት በፊት ያለው ሐሙስ ነው። ይህ ዕለት «ዕለተ ሐሙስ» ይባላል። በዚህ ዕለት በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የአዲስ ኪዳን መስዋእት ተመስርቶልናል። (ማቴ 26፥26 ። ማር 14፥22 ። ሉቃ 22፥19) በዚህም ዕለት ቅዳሴ መቀደስ እንዳለበት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ያዛል። ከቅዳሴ ቀደም ብሎ ካህኑ የምእመናኑን እግር በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያጥባሉ። ጌታ የጸሎተ ሐሙስ ዕለት

የሐዋርያትን እግር ተንበርኮ የማጠብና የትህትናው መታሰቢያ ነው። ዮሐ 13፥1-18

## *ዕለተ ስቅለት*

ከጸሎተ ሐሙስ ቀጥሎ ያለው ዕለት ዕለተ ዓርብ ነው። ይህም ዕለት ስቅለት ይባላል። በዚህ ቀን የጌታ የስቅለቱና የመከራው ሁሉ መታሰቢያ ዝግጅት ይደረጋል። የስቅለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሁሉ ሲነበቡ ይውላሉ። ስግደቱም ከሰሞኑ የበለጠ ነው። ሰርክ (11 ሰዓት) ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን በሰሞነ ሕማማት ውስጥ የሠራውን ኃጢአት ወደ ካህኑ በመቅረብ ይናዘዛል። ካህኑም የወይራ ቅጠል እየጠበጠቡ ተጨማሪ ጸሎትና ስግደት ለምእመኑ በመስጠት ፈጣሪውን ይቅርታ እንዲጠይቅ ያዛሉ። ምእመኑም ትእዛዙን ተግባራዊ በማድረግ ከፈጣሪው ይቅርታና ምሕረትን እንዳገኘ ያምናል። … ያዕ 5፥16 ከዚህ በኋላ ምእመናኑ በደስታ መንፈስ ተሞልተው ወደ የቤታቸው ይመለሳሉ። ይህም በቤተ ርስቲያናችን በየዓመቱ በናፍቆት የሚጠበቅ ሥርዓት ነው።

## *ቀዳም ስዑር*

ከስቅለት ቀጥሎ ያለው ቀን ቅዳሜ ነው። ይህም ዕለት ቀዳም ስዑር ይባላል። የተሻረ የተባለበትም ምንያት ከዓመት እስከ ዓመት ባሉት ቅዳሜዎች ጦም አይጦምባቸውም፤ ምክንያቱም የጦም ጊዜ እንኳ ቢሆን ቅቤና ሥጋ ይቀራል እንጂ ሌላውን ምግብ ቅዳሜና እሁድ መጦም ክልክል ነው። በዚህ ዕለት ግን እስከ ትንሣኤ ድረስ ጧትም ማታም እህል ውኃ አይቀመስም ይህም አፍሎት ይባላል። በዚህ ምንያት የተሻረ ለማለት «ቀዳም ስዑር» ተብሎአል።

## 2ኛ. *ጾመ ሐዋርያት*

ከዓቢይ ጾም ቀጥሎ ሁለተኛው ጾም «ጾመ ሐዋርያት» (የሰኔ ጾም) ይባላል። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ከመሰማራታቸው በፊት የጾሙት ጾም ነው። በዚህም የወንጌል ሥራቸው ሰምሮላቸዋል። ስለዚህ አልጫ የነበረውን ዓለም በወንጌል ለማፋጠን ሐዋርያት ከጾምና ከጸሎት ጋር የቱን ያህል እንደተጋደሉና መንፈስ ቅዱስም በሐዋርያት አድሮ የሠራውን ድንቅ ሥራ ለማሰብ ሲሆን፥ ዛሬም በሐዋርያት ድካም በእግዚአብሔር ቸርነት የተመሠረተች እግዚአብሔርን በጾም ለመለመን ነው ክርስቲያኖች በየዓመቱ ይህን ጾም የሚጾሙት። ይህ ጾም በመባጃ ሐመር (አቆጣጠር) ከፍና ዝቅ ሊል ስለሚችል የተወሰነ ቀን የለውም። አንዳንድ ጊዜ ከአርባ ቀን ይበልጣል። አንዳንድ ጊዜም ከሠላሳም ያንሳል።

## 3ኛ. *ጾመ ፍልሰታ*

የዚህ ጾም ቀን የተወሰነ ነው። ይህም ከነሐሴ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 15 ቀን ያለው ብቻ ነው። ይህ ጾም የእመቤታችን መታሰቢያ ነው። በተለይም ታሪኩ በትንሣኤዋና በእርገቷ ላይ ያተኩራል። ይኸውም ባጭሩ ቅዱሳን ሐዋርያት የእመቤታችንን አስከሬን በጸሎትና በምሕላ በቀበሩ ጊዜ ሐዋርያው ቶማስ ለተልዕኮ እንደሄደ ስላልተመለሰ አልነበረም። ሆኖም እመቤታችን ከሞት ተነስታ በክብር ወደ ገነት ስታርግ እሱ ደግሞ በተኣምር ሲመለስ ተገናኝተው የከፈኗን ጨርቅ ለበረከት ሰጥታዋለች። ይህንም የምስራች ለሐዋርያት ነግሯቸው ለማስረጃም ያህል ለበረከት የሰጠችውን ጨርቅ አሳይቷቸዋል። በዚህ ጊዜ የቶማስ እመቤታችንን የማየት እድል እንዲደርሳቸው በማቴ 7፥7 «ለምኑ ይሰጣችኋል፥ ፈልጉ ታገኛላችሁ» ባለው መለኮታዊ ቃል መሰረት ከነሐሴ 1-15 ቀን በጾም ለምነውት ክርስቶስም ለጥያቄያቸው መልስ ሰጥቷቸዋል ማለትም እመቤታችንን ለማየት በቅተዋል። ስለዚህ ይህን ድንቅ ነገር ለማሰብና ይህን ጾም ምክንያት በማድረግ የተሰወረው መንፈሳዊ ምስጢር ሁሉ በቸርነቱ ለቤተ ክርስቲያን የተገለጠ እንዲሆን በማለት ምእመናን በየዓመቱ ጾመ ፍልሰታን ይጾማሉ።

## 4ኛ ጾመ ነቢያት (የገና ጾም)

አራተኛው የጾም ወራት ጾመ ነቢያት (የገና ጾም) ይባላል። ይህ ጾም ከሕዳር 15 እስከ ታኅሣሥ 28 ያለው ጊዜ ነው። የጾሙ ወራት 43 ቀን ነው። ልደት፥- በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ 28 ቀን ይውላል። በዚህ ዓመት በጾሙ በፊት ቅበላ ሕዳር 14 ቀን ይሆናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከመገለጡና ሰው ከመሆኑ በፊት ነቢያት የጌታን መምጣት በናፍቆት በጾምና በጸሎት ሲጠባበቁ ነበር። ስለዚህ የነቢያትን የጾም ድካም ለማሰብና አሁንም የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ደግሞ የሚመጣ ክርስቶስን በናፍቆት ሲጠባበቁ እንደ ነቢያት መንፈስ ኃይልን ለመልበስ፤ በእምነት ለመጽናት፤ ኃጢአትን ለመዋጋት ሲባል ይህን ጾም ክርስቲያኖች ይጾሙታል።

## 5ኛ. ገሃድ

ገሃድ ማለት ግልጥ የሆነ ለውጥ ማለት ነው። ገሃድ የጥምቀት ብቻ ነው። ይኸውም ጥምቀት ረቡዕና ዓርብ ቀን በሚውልበት ጊዜ በኋላው የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስ የፍስክ ቀንነታቸው ወደ ጾምነት ተለውጦ ይጾማሉ። በነሱ ለውጥ ጥምቀት የሚውልባቸው ቀኖች ማለትም ረቡዕና ዓርብ የፍስክ ቀን ሆነው ይውላሉ። ሆኖም ጥምቀት በሌላም ቀን ቢውል የዋዜማው ቀን ይጾማል። ቅዳሜና እሁድ እንኳ ቢሆኑ ለምሳሌ ጥምቀት እሑድ ቀን ቢውል ቅዳሜ ሥጋና ቅቤ አይበላም። ጥምቀት ሰኞ ቢውል ደግሞ እሑድ ሥጋና ቅቤ አይበላም። እንደ ሌሎች ቀኖች ግን ከማንኛውም ምግብ ጦም አይዋልም። የልደት ዋዜማ የሆኑት ቀኖች ግን ምንጊዜም ከጾመ ነቢያት ጋር የተያያዙ ስለሆኑና ስለሚጾሙ በልደት ገሃድ የለም። በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች የገናን ጾም ሲበሉ ቆይተው በልደት ዋዜማ አንድ ቀን በመጾም እንደገሃድ ይቆጥሩታል። ይህም የግለሰቦች እንጂ በቤተ ክርስቲያን የተወሰነ አይደለም።

## 6ኛ. ነነዌ ጾም

የዚህ ጾም ጊዜ ሦስት ቀን ብቻ ነው። ቀኖቹም በየዓመቱ ሰኞ ማክሰኛና ረቡዕ ናቸው። የነነዌ ጾም በመባጃ ሐመር (አቆጣጠር) ከፍና ዝቅ ስለሚል አንድ ጊዜ በጥር አንዲ ጊዜ በየካቲት ይሆናል። የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን ጾም የወሰኑት፥- ልትጠፋ የነበረች ነነዌን በጾም ምክንያት እግዚአብሔር ይቅር ስላላት፥- ይህን አምላካዊ ይቅርታውን ለዘለዓለም ለማሰብና ዛሬም በዚህ ዓለም ከነነዌ የከፋ ርኩሰትና ኃጢአት ስላለ የነነዌን ሕዝብ ይቅር ያልክ አምላክ ዛሬም ይቅር በለን ለማለት ነው።

## 7ኛ. የረቡዕና ዓርብ ጾም

ሰባተኛውና የመጨረሻው ጾም ረቡዕና ዓርብ ነው። አይሁድ ክርስቶስን በእንጨት ሰቅሎ ለመግደል የተፈራረሙበት ዕለት ረቡዕ ነው። ዓርብ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ይህ ነው የማይባል ጽዋትወ መከራና ተገፍዖ የተቀበለበት፥ የተሰቀለበትና የሞተበት እኛም የዳንንበት ቀን ነው። ስለዚህ፥-

1ኛ. የጌታን መከራና ስቃይ ለማሰብ

2ኛ. ዛሬም ቤተ ክርስቲያንን የሚገፉ ክርስቲያኖችን ለመበተን በስብሰባ የሚፈራረሙ እምነትን ለማጥፋት የሚጥሩ ስላሉ የመለኮት ኃይል ይህን ሁሉ የፈተና ማዕበል እንዲያስወግድ ክርስቲያኖች በየሳምንቱ ረቡዕና ዓርብን ያለመሰልቸት ይጾማሉ።

በተለይ ዓርብ ሲጠበቅ የነበረው የመዳን ተስፋ የተፈጸመበት ቅዱስ ዕለት በመሆኑ በጾም መከበሩ ሲያንስ ነው። በሌላ በኩል ግን ከትንሳኤ ጀምሮ እስከ በዓለ ሃምሳ ድረስ ባሉት ቀናት ውስጥ የሚገኙት ረቡዕና ዓርብ ፍስክ በመሆናቸው አይጾሙም። እነዚህ ሃምሳ ቀናት በአርባ ጦም

ስለተጎዳው የምእመናን ሰውነት የእረፍትና የመታደስ ቀናት ናቸውና። በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከተወሰኑት ከነዚህ ሰባት አጽዋማት ሌላ በፈቃድ የሚጾሙ ጽጌ ጾምና ጻጉሜን የሚባሉ አሉ። ጽጌ ጾም ከመስከረም 25 እስከ ሕዳር 5 ቀን ሆኖ በጠቅላላው አርባ ቀን ነው። በመስከረም ማለትም በአበባ ወራት ስለሚጾምና እመቤታችንም በአበባ ስለምትመሰል፤ ጾሙ የጽጌ ጾም ይባላል። ይህ ጾም እመቤታችን ወደ ግብጽ የመሰደድዋ መታሰቢያ ነው። ከዚህም ሌላ የዓመቱን መጨረሻ ጻጉሜን የሚጾሙ አሉ። ይህም የሚቀጥለውን አዲስ ዓመት ባርክልን ለማለት ነው። የዚህ የጾም ጊዜ በዘመነ ዮሐንስ 6 ቀን ከሚሆን በቀር፡- በየዓመቱ መጨረሻ 5 ቀን ብቻ ነው።

በበረሃ ያሉ መነኮሳትና ባሕታውያን ግን በቀኖና ከተወሰኑት ከሰባቱ አጽዋማት ሌላ ዓመት እስከ ዓመት ይጾማሉ። ብዙዎች ምእመናንም እንዲሁ በግል ኃጢአታቸው ንስሃ በመግባት ለባልንጀሮቻቸው ችግርና ፈተና መወገድ፤ ለዓለም ሰላም፤ ላገር መጠበቅ ለቤተ ክርስቲያን ደህንነት፤ ለምእመናን የእምነት ጥንካሬ ሲባል፡- ማንም ሳያውቅ በግልና በስውር የሚጦሙ አሉ። ለዚህ ነው ጸሎት፤ ጦም፣ ምጽዋት እነዚህ ሦስቱ የማኅበርና የግል፤ የግልጥና የስውር ተብለው በሁለት የሚከፈሉት።

## የአዲስ ኪዳን ጾም አመሠራረት

የአዲስ ኪዳንን ጾም የመሠረተልን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማቴ 4፤1 ሉቃ 4፤1 አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ጾምን መመሥረት ብቻ ሳይሆን፤ ዲያብሎስንና ከልጅነት ጀምሮ ተቆራኝቶ የሚያድገውን ክፉ መንፈስ ሁሉ ማላቀቂያው ጾም መሆኑን በማቴ. 17፤14-21 ተናግሯል።

በዚህ አምላካዊ ቃል መሠረት አብሮን ተቆራኝቶ ካደገ ከልዩ ልዩ የመጥሮ ሱስ ክፉ መንፈስ ልንላቀቅ የምንችለው፡- በተሰበረ ልቡና በእውነተኛ ንስሃ ሆነን በምንጠቀምበት ክርስቲያናዊ ጾም ነው። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ጾም ሰው ሰራሽ ሳይሆን ፈተናን ሁሉ ለማለፍ የምንጠቀምበት መንፈሳዊ ኃይል በመሆኑ አክብረን ልንይዘው ይገባል።

### የጾም ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

1ኛ. በጾም ወራት የዓሣን ሥጋ የሚመገቡ አሉ ስለዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

መልስ፡- መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ጾም ሥጋን የማድከምና ሥጋዊ ፍትወትን የመቆጣጠር ጥበብ ነው። እንዲያውም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መረጃነት ከሆነ ጾምን ይጾሙ የነበሩ አባቶች በአብዛኛው ያለምንም እህል ውሃ ነው። ዘጸ 34፤27፣ መጽ. አስቴር 4፤13፣ ዮናስ 3፤10- ፍጻሜ፣ ማቴ 4፤1-4፣ሉቃ 4፤1። ይሁን እንጂ ያለምንም እህል ውሃ መጾም ለማይችሉ ደግሞ ከሥጋ ከቅቤና ከሚያስክር መጠጥ ከማለፊያ እንጀራ ሳይቀር ተከልክለው በመናኛ ምግብ ማለትም ለሥጋ ኃይል ሰጭ ያልሆኑ ምግቦችን በመውሰድ መጾም እንደሚችሉ ይናገራል። መዝ 108፤23-25፣ ዳን 9፤3፣ ዳን 10፤2 ከዚህ ውጪ በጾም ጊዜ የዓሣ ሥጋ ብሉ የሚል የለም።

2ኛ. ሀ) ጌታ የጸሎት ሐሙስ ዕለት ሐዋርያቱን የዓሣ ሥጋ መግቧል።

ለ) በፍትህ መንፈሳዊ (በፍትሐ ነገሥት) ስለ ጾም በሚናገርበት ክፍል «ኢትብልዑ ሥጋ ዘእንበለ ዓሣ» ይላል። ስለዚህ ጌታ የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ሐዋርያቱን የዓሳ ሥጋ ከመገበ፤ ፍትሐ ነገሥቱም «በጾም ጊዜ ሥጋ አትብሉ ከዓሣ በቀር» ካለ በጾም ወራት ዓሣ የማይበላበት ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ፡- በቅድሚያ የጸሎተ ሐሙስ ዓሣ ጉዳይ፡- የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ሐዋርያት የዓሣ ሥጋ በመመገባቸው ጾምን አልሻሩም። ምክንያቱም የአዲስ ኪዳን ጾም የተጀመረው ከጌታ ሞትና ትንሣኤ እንዲሁም ከእርገቱና ከመንፈስ ቅዱስም መውረድ በኋላ ነውና። ጌታ ሐዋርያቱን የመገበው ግን

የስቅለት ዋዜማ ሐሙስ ዕለት ከመሞቱ በፊት ነው። ስለዚህ ከአዲስ ኪዳን ጾም ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ከጌታ ሞት በፊት ሐዋርያት እንደማይጾሙ ከጌታ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ግን እንደሚጾሙ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጦመው ደቀመዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ስለምንድን ነው? አሉት ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፣ ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ሰዓት ይመጣል በዚያ ጊዜም ይጦማሉ በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚያኖር የለም መጣፊያው ልብሱን ይቦጭቀዋልና መቀደዱም የባሰ ይሆናል። በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም ቢደረግ ግን አቁማዳው ይፈነዳል የወይን ጠጁም ይፈስሳል፤ አቁማዳውም ይጠፋል ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ የአኖሩታል፤ ሁለቱም ይጠባበቃሉ» ይላል ማቴ 9፥14-18

በዚህ ምንባብ ውስጥ ሙሽራ የተባለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሚዜዎች የተባሉም ሐዋርያት ናቸው። ሙሽራው የሚወሰድበት ቀን የተባለው ደግሞ ዕለተ ዓርብ የጌታ መስቀል ቀን ነው። ስለዚህ ሙሽራ የተባለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከሞተና ከተቀበረ ከተነሳና ከዐረገ በኋላ ይጦማሉ ለማለት ነው ትክክለኛው ይኸው ነው። አሮጌ አቁማዳ ማለትም የአዲስ ኪዳን ሥርዓት ያስረጀው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ነው። አዲሱ የወይን ጠጅም ክርስቶስ ራሱና በክርስቶስ ደም የከበረው ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው። ስለዚህ የዮሐንስ ደቀመዛሙርትና ፈሪሳውያን የሚጦሙት ወደ ታይታና ወደ ግብዝነት እየተለወጠ የመጣው የብሉይ ኪዳን የጾም ሥርዓት አክትሞ፣ በክርስቶስ አዲስ የሆነ የአዲስ ኪዳን ጾም በአዲስ ኪዳን እንደሚመሰረት ለማስረዳረት በምሳሌ «ማንም አዲስ የወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ማስቀመጥ የሚችል የለም አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖሩታል እንጂ» በማለት ተናግሮአል። ስለዚህም ነው በ 2ኛ ቆሮ 5፥17 ላይ «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው። አሮጌው ነገር አልፏል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል» በማለት ያስተማረን።

በተጨማሪም በማቴ 17፥14-22 ላይ ታሪኩ እንደሚናገረው ሐዋርያት ሊያስለቅቁት ያልቻሉ በአንድ ብላቴና ላይ የነበረ ክፉ ጋኔን ነበር። ጌታ ግን ጋኔኑን ገሰጸውና አባረረው፥ ልጁም ተፈወሰ በዚህ ጊዜ ሐዋርያት ጌታን ስልጣን ሰጥተኸን ተአምራትም ስናደርግ ቆይተናል አሁን ይህ ጋኔን እንዴት ሊያሸንፈን ቻለ? ብለው ጠይቀውት «የዚህ ዓይነት ጋኔን በጦምና በጸሎት ነው የሚባረረው» በማለት አስረድቷቸዋል። ስለዚህ ይህ አባባል ሐዋርያት ከጌታ ጋር ሳሉ ገና ጦም አለመጀመራቸውን ያረጋግጣል። ከጌታ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ግን ጦም መጀመራቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ሐዋ 13፥2-3፣ 14፥23፣ 2ቆሮ 6፥6

ለ) «ኢትብልዑ ሥጋ ዘእንበለ ዓሣ» ኢትብልዑ ማለት አትብሉ ማለት ነው። ሥጋ ያው ሥጋ ነው። ዘእንበለ የሚለው የግእዝ ቃል ግን ቃሉ አንድ ሆኖ ሦስት ፍች አለው ይከውም፦-

1ኛ ዘእንበለ = ያለ

2ኛ ዘእንበለ = በቀር

3ኛ ዘእንበለ = ሳይቀር ተብሎ ይፈታል። አሁን እንግዲህ «ኢትብልዑ ሥጋ ዘእንበለ ዓሣ» የሚለውን ትርጓምያኑ ሲተረጉሙ «ሥጋን አትብሉ ያለ ዓሣ በቀር» ብለው ስለተረጎሙት በጾም ጊዜ ለብዙ ዓመታት የዓሣ ሥጋ እንደ ዓይነተኛ ምግብ ሆኖ ቆይቶአል። ነገር ግን የግእዙ ባለሙያ የሆኑትና በተለይም መንፈሳዊ ሕይወትና ብስለት ያላቸው አባቶች «ኢትብልዑ ሥጋ ዘእንበለ ዓሣ» የሚለውን «በጾም ጊዜ ሥጋ አትብሉ ዓሣ ሳይቀር» ብለው አቃንተው በመተርጎም አስተካክለውታል። ደግሞስ በጾም ጊዜ የዓሣ ሥጋ ከተበላ የበሬው፣ የፍየሉ፣ የበጉና የዶሮው ሥጋ ምን አደረገ? በማለት ተችተዋል፣ እውነቱም ይኸው ነው። ምክንያቱም የዓሣ ሥጋ ከሌሎች የሥጋ ምግቦች እጅግ የበለጠ ለመሆኑ የዘመኑ ጠበብት መስክረዋል። ጾም ደግሞ ከኃጢአትና ከክፉ ነገር መሸሽ ማለት ሲሆን የመጀመሪያው ጀረጃ ግን ሥጋን ከአልሚና ኃይል ሰጪ ከሆኑ ምግቦች ከልክሎ ማድከም ነውና።

3ኛ . ከአፍ የሚወጣ እንጂ የሚገባ አያረክስም፣ ማቴ 15፥1-3 እንደተጻፈው በሙሴ ሥርዓት እጅን ሳይታጠቡ መብላት ያረክሳል ስለሚልና ሐዋርያት ደግሞ ከስራ ብዛት የተነሳ አንዳንድ ጊዜ እጃቸውን

ሳይታጠቡ መብላት ያረክሳል ስለሚልና ሐዋርያት ደግሞ ከሥራ ብዛት የተነሳ አንዳንድ ጊዜ እጃቸውን ሳይታጠቡ ሲበሉ ፈሪሳውያን ተመልክተው ጌታን ጠይቀውታል። ጥያቄውም «ደቀመዛሙርትህ የአባቶችን ሥርዓት እያፈረሱ ነው እጃቸውን ሳይታጠቡ ይበላሉና ይህ ለምን ሆነ?» ብለው ጠይቀውት ጌታም «ሕዝቡን ሁሉ ጠርቶ ስሙ! አስተውሉም፤ ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባው አይደለም የሚወጣው እንጂ» ማቴ 15፥10 በማለት የተናገረውን ምክንያት በማድረግ «በጾም ጊዜ እንኳን ዓሣ፥ ሥጋና ቅቤ የማንበላበት ምክንያት ምንድን ነው? ጌታ ወደ አፍ የሚገባው አያረክስም ብሏልና» የሚሉ አሉ። ይህ ብቻ አይደለም

ሀ) በ1ኛ ጢሞ 4፥4 «እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል የሚከለክሉ አሉ፥ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና።»

ለ) በ1ኛ ቆሮ 10፥25 «በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ከኅሊና የተነሳ ሳትመራመሩ ብሉ ምድርና በእርሷ የሞላባት ሁሉ የጌታ ነውና።»

ሐ) ወደ ቲቶ 1፥15 «ሁሉ ለንጹሖች ንጹህ ነው ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹህ የሆነ ምንም የለም» የሚለውንና የመሳሰለውን በመጥቀስ፥- በጾም ጊዜ ሥጋና ቅቤ አይበላም ወተትም አይጠጣም የምትለውን ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን እንዳልተቀበለች አድርገው የሚኮንኗትና በጾም ጊዜ የፈለግነውን መመገብ አለብን የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ለዚህም መልስ አለ?

<u>መልስ</u>፥- መልሱ ቀላል ነው። ይኸውም እኛ በጾም ጊዜ ሥጋና ቅቤ ማለትም የተከለከሉ ምግቦችን የማንወስደው እነዚህን ምግቦች ለሥጋችን ኃይልን እንዲሰጡ የበለጠ ስለ ባረካቸውና በጾም ጊዜ እነዚህን ምግቦች ብንወስድ ሥጋችን ኃይል ያገኝና ሥጋዊ ሥራን ያሰራናል፥ ጾም ማለትም ሥጋን አድክሞ ኃጢአትን ማሸነፍ በመሆኑ የጾምነት ትርጉሙን ያጣል፥ በመጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን በፊት እንደ ተማርነው እንደዚሁ በመሆኑ እንጂ እነዚህ ምግቦች ያረክሱናል ብለን አይደለም። እነዚህ ምግቦች ርኩሳን ናቸው ብንል ኖሮ ይህ ሁሉ የጥቅስ ብዛት በተጠቀሰብን ነበር። ነገር ግን ያረክሱናል ብለን አናምንም።

4ኛ. «ስትጦሙ እንደግብዞች አትጠውልጉ፥ ለሰዎች እንደጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠወልጋሉና እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ፥ ፊትህንም ታጠብ በስውር የሚያይ አባትህ በግልጥ ይከፍልሃል» ይላል። ማቴ 6፥6 ይህ ከሆነ እኛ ለምን በግልጥ ሰው እያወቀ እንጦማለን?

<u>መልስ</u>፥- ጌታ ይህን ቃል የተናገረው ጾምን ስትጾሙ እንደ ፈሪሳውያን ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለሰው አታድርጉት፥ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ተመልክታችሁ አድርጉት ለማለት ነው። በተጨማሪም ጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት እንዚህ ሦስቱ፥- በግልና በስውር፥ በግልጥና በማኅበር መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። በስውር ብቻ ከሆነማ፥- የጌታ አርባ ቀን መጦም የሐዋርያትና የቀደሙ ክርስቲያኖች በማኅበርና በግልጥ መጦማቸው ባልተጻፈም ነበር።

አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ